# በበርሊን የኢፌዲሪ ኤምባሲ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት መለየትን ተከትሎ የሐዘን መግለጫ ሥነ-ሥርዓት ተካሄደ



ከመንግሥት በተላለፈው መመሪያ መሠረት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ህልፈት ምክንያት ዜና ዕረፍታቸውን ከተሰማበት ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ስርዓተ ቀብሩ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሐዘን ቀን ሆኖ እንዲቆይ መወሰኑ ተከትሎ በበርሊን የኢፌዲሪ ኤምባሲ የሐዘን ስነ-ስርዓት ተካሂዷል፡፡

ይህንንም ምክንያት በማድረግ በኤምባሲያው ከማክሰኞ  ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ሰንደቅ ዓላማ በግማሽ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ የተደረገ ሲሆን ከነሐሴ 22 ቀን 2004  እስከ ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ መንግሥት ተወካይ፣ በበርሊን የሚገኙ የዲፕሎማቲክ፣ የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም በኢ-ሜይልና በፖስታ ከደረሱን በርካታ የሐዘን መግለጫዎች በተጨማሪ በበርሊንና በአካባቢው ከተሞች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ-ኢትዮጵያውያን በተዘጋጀው የሐዘን መግለጫ ሰነድ ላይ በመፈረም ሐዘናቸውንና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበራቸውና ፍቅርና አድናቆት ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻው ቀን በበርሊንና በአካባቢዋ የሚገኙ  ኢትዮጵያውያንና ትውልድ-ኢትዮጵያውያን በተገኙበት የሻማ ማብራት ስነ ስርዓት በማድረግ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አመራር ሰጪነት የተጀመሩ የሰላም፣ የዲሞክራሲና የልማት ዕቅዶች እንዲሁም ኢትዮጵያን ከበለጸጉ ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የነበራቸውን ራዕይ ለማሳካት የቃል መግባት ስነ-ስርዓት ተደርጓል፡፡ በተለይም በበርሊን ተቋቁሞ በመስራት ላይ የሚገኘው የህዳሴው ግድብ መማክርት አባላት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ኢትዮጵያ በለውጥ ሽክርክሪት ውስጥ እንድትገባ የከፈሉት መስዋዕትነት ለቀጣይ ትውልዶች አርዓያ የሚሆንና ይህም

የለውጥ ችቦ ኢትዮጵያ ወደ ብልፅግና እስከትሸጋገር ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚቀጥል መሆኑን ገልፀው በሳቸው በሳልና አመራር የተጀመሩ ስራዎችን ከግብ ለማድረስ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለመወጣት ቃል ገብተዋል፡፡

በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሚሲዮኑ መሪ ክቡር አምባሳደር ፍስሐ አስገዶም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከወጣትነት የትምህርት ቤት ውሎ እስከ ትግል ሜዳ ቀጥሎም በመንግሥት አመራር በሰሩበት ጊዜ የነበረውን ሁሉ በማስታወስ ጠቅላይ ሚኒሰትራችን ምን ያህል ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ቀናኢ እንደነበሩ፣ የሚሰሩትን ሁሉ በላቀ የዕውቀት ደረጃ በተደገፈ ሁኔታ የሚወጡ፣ በሀገራቸው ጥቅም ላይ የማይደራደሩና ለበርካታ ኢትዮጵያዊን ተምሳሌት የሚሆኑ የተዋጣላቸው ታጋይ መሪ እንደነበሩ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የእርሳቸውን ታላቅ አመራርነትና ገድል እንዲሁ በአጭሩ ማስቀመጥ እንደማይቻልና ወደፊት ታሪክ በሰፊው የሚዘክረው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ኤምባሲውም በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ-ኢትዮጵያውያን በማስተባበር በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ  የተጀመሩ የልማት ውጥኖችን ከግብ ለማድረስ በትጋት እንደሚሰራና ለዚህም ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ከአደራ ጭምር አሳስበዋል፡፡

በዕለቱ የተገኙት ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን በመግለጽ ለሀገራቸው ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት ቃል የገቡ ሲሆን ለቤተሰቦቻቸውና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን ተመኝተዋል፡፡

ነሐሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም
የኢፌዲሪ ኤምባሲ
በርሊን